የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አርባምንጭ ታህሳስ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት
ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 25
Arba minch December 15 ቀን 2023

| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| አዋጅ ቁጥር ፳፰/፪ሺ፲፮ ዓ.ም<br>የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ገፅ--- | Proclamation No. 28/2023<br>Proclamation of the **ENVIRONMENTAL IMPACT ASSESSMENT** of the South Ethiopia Regional State---Page . |

**አዋጅ ቁጥር ፳፰/፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ**

**PROCLAMATION NO. 28/2023**

**ENVIRONMENTAL IMPACT ASSESSMENT PROCLAMATION OF SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE**

## መግቢያ

በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች የሚደረጉ ዘርፈ ብዙ የልማት እንቅስቃሴዎች ከአገሪቱ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተግባራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አንድ የልማት ሀሳብ ንድፍ ሲዘጋጅ፣ ቦታው ሲመረጥ፣ ተግባር ላይ ሲውል እና በመተግበር ላይ ያለ እንቅስቃሴ ሲሻሻል ወይም ሲቋረጥ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ በመተንበይና አስቀድሞ በማረም የታሰበዉን ልማት ለማምጣት የሚያግዝ በመሆኑ፤

## Preamble

WHEREAS, it is necessary to implement diverse development activities across the region that align with the country's green development strategy;

WHEREAS, environmental impact assessment is used to predict and manage the environmental effects which a proposed development activity as a result of its design setting, site selection, and implementation, or an ongoing activity as a result of its modification or termination, entails and thus helps to bring about intended development;

የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቶች አካባቢን በመጠበቅ በተለይም የህብረተሰቡን ጤንነት፣ የህያዋን ደህንነትና የተፈጥሮ ሥነ ውበትን በጠበቀ መልኩ መተግበር ያለበት በመሆኑ፤

WHEREAS, the implementation of socio economic developments must be carried out in a manner that protects the environment, in particular, safeguarding of communities health as well as well-being, maintaining of the biota , and the aesthetis of value nature;

የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አስተዳደራዊ ግልጽነትና በኃላፊነት ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ በአጠቃላይ ራሱንና አካባቢውን በሚመለከቱ የልማት እቅዶች አወጣጥና ውሳኔ ላይ ሕዝቡን በተለይም ደግሞ ማህበረሰቦችን ለማሳተፍ የሚረዳ በመሆኑ፣

WHEREAS, environmental impact assessment serves to bring about administrative transparency and accountablity, as well as to involve the public and, in particular, communities in the planning of and decision taking on developments which may affect them and its environment;

አሉታዊ የአካባቢ ተጽዕኖዎችን በመተንበይ የመፍትሄ እርምጃዎችን መውሰድና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸውን ማዳበር በፌደራል እና በክልሉ ሕገ መንግሥት የተደነገጉትን የአካባቢ ደህንነት መብቶችና አላማዎችን የመተግበርና የማስፈጸምን ሂደት የሚያግዝ በመሆኑ፣

WHEREAS, the implementation of the environmental rights and objectives enshrined in the Federal and Regional Constitution would be fostered by the prediction and management of likely adverse environmental impacts, and the maximization of their socio-economic benefits.

የልማት ፕሮጀክቶች ሲዘጋጁ ከፕሮጀክቱ የሚከሰቱ አሉታዊ ተጽዕኖን አስቀድሞ በመገምገም የመከላከያ ወይም መቀነሻ እርምጃዎች አወሳሰድን በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, enshrinement of taking prevention or minimization measures in the law is required while carrying out prior impact assessment of the development projects that are likely to have adverse impact;

የክልሉን ነባራዊና ተጨባጭ እውነታን ያገናዘበ ክልላዊ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት ለዘላቂ ልማት መስፋፋት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ በመታመኑ፤

WHEREAS, establishing environmental impact assessment system that considers the existing and observable realities of the region is important for the expansion of sustainable development.

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፬ ንዑስ አንቀጽ ፫(ሀ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

NOW, THEREFORE, in accordance with the sub-article 3/a/ of Article 54 of the Constitution of the Region, Concil of South Ethiopia Region issued this proclamation.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር ፳፰/፪ሺ፲፮” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር:-

፩.“ክልል” ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነው፡፡

፪.“ቢሮ” ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደን አካባቢ ጥበቃና ልማት ቢሮ ነው፡፡

፫.“አከባቢ” ማለት በመሬት ፣ በከባቢ አየር ፣ በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት ፣ በውሀ ፣ በህያዋን : በድምጽ: በሽታ በጣዕም : በማህበራዊ ጉዳዮች እና በሥነ ውበት ሳይወሰን በተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና በያሉበት በታ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸው ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ህያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ መስተጋብሮቻቸው ድምር ነው፡፡

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short title

This proclamation may be cited as "South Ethiopia Regional State Environmental Impact Assessment Proclamation No. 28/2023.

### 2. Definitions

Unless the context requiary otherwise, in this proclamation:-

1. "Region" means South Ethiopia. Region

2."Bureau" means Forest Environment Protectiona and Development Bureau of South Ethiopia Regional State

3. "Environment" means the totality of all materials whether in their natural state or modified or changed by human; their external spaces and the interactions which affect their quality or quantity and the welfare of humans or other living beings, including but not restricted to, land atmosphere, whether and climate, water, living things, sound, odor, taste, social factors, and aesthetics;

፬."አካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ" ማለት አንድ ፕሮጀክት ወይም የመንግሥት ሰነድ ተግባራዊ ሲሆን የሚያስከትለውን ገንቢም ሆነ አፍራሽ ውጤት በቅድሚያ ከመተግበሩ በፊት ለይቶ የማወቂያና የመመዘኛ ዘዴ ነው።

፭."ተፅዕኖ" ማለት በአጠቃላይ ሲታይ በአካባቢያዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ ወይም በባህላዊ ሁኔታ ላይ የሚከሰት አሉታዊ ለውጥ ነው።

፮."ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት" ማለት በክልሉ ውስጥ የስራ ፈቃድ ለመስጠት ወይም የንግድ ድርጅቶችን ለመመዝገብ በሕግ ስልጣን የተሰጠው ማንኛውም አካል ነው።

፯."በካይ" ማለት ፈሳሽ ፣ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ በቀጥታም ይሁን ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ:-

ሀ/ ያረፈበትን የአካባቢ ጥራት በመለወጥ ጠቀሜታ የመስጠት አቅሙን የሚያጓድል ወይም

ለ/ በሰው ጤና ወይም በሌሎች ህያዋን ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል መርዝን ፣ በሽታን፣ ክርፋትን ፣ ጨረርን ፣ ድምጽን ፣ ንዝረትን ፣ ሙቀትን ወይም ሌላ ክስተትን የሚያመነጭ ማንኛውም ነገር ነው።

፰."ፕሮጀክት" ማለት በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ ውስጥ በተጠቀሰ ርዕስ የሚካተት ማንኛውም አዲስ የልማት እንቅስቃሴ ወይም በነባር ድርጅት ላይ የሚደረግ ጉልህ መስፋፋት ወይም ለውጥ ወይም ደግሞ ተቋርጦ የነበረን ስራን መልሶ ለመጀመር የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው።

4. "Environmental Impact Assessment" means the methodology of identifying and evaluating in advance any effect, be it positive or negative, which results from the implementation of a proposed project or public instrument;

5. "Impact" means generally consideration of any change that may affect environmental, social, economic, or cultural conditions;

6. "Licensing Office" means any organ empowered by law within the region to issue a work permit or to register a business organization::

7. "Pollutant" means any substance whether liquid, solid or gas which directly or indirectly:

A/ alters the quality of the receiving environment so as to affect its beneficial use adversely, or

B/ produces toxic substances, diseases, objectionable odour, radioactivity, noise, vibration, heat, or any other phenomenon that is hazardous or potentially hazardous to human health or to other living things.

8. "Project" means any new development activity under any category listed in regulation or directive issued pursuant to this Proclamation and following this Proclamation, major expansion or alteration or any existing undertaking, or any resumption of work that had been discontinued:

፱.“የፕሮጀክት ባለቤት” ማለት ፕሮጀክቱ በክልሉ መንግሥት የተወጠነ ሲሆን የሚመለከተው የክልሉ መንግሥት አካል ወይም በግሉ ዘርፍ የተወጠነ ሲሆን ባለሀብት የሆነው ሰው ነው፡፡

9. "Proprietor" means any organ of the regional government if in the public sector or any person if in the private sector that initiates a project;

፲.“መንግሥታዊ ሰነድ” ማለት ፖሊሲ ፣ ስልት ፣ መርሀ-ግብር ፣ ሕግ ወይም የዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፡፡

10. "Public instrument" means a policy, a strategy, a programme, a law or an international agreement;

፲፩.”የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ሰነድ” ማለት በፕሮጀክት ባለቤት ለማህበራዊና ለአካባቢያዊ ደህንነት ሲባል የሚወሰድ እርምጃ በተመለከተ ለቢሮ የሚቀርብ የጥናት ሰነድ ነው፡፡

11. "Environmental impact study instrument" means the study instrument submitted to the bureau by the Proprietor, outlining measures designed to ensure social and environmental well-being.

፲፪.“የይሁንታ ፈቃድ” ማለት በቢሮው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ዘገባውን መርምሮ የአካባቢ ተፅዕኖውን ለመቀነስ ወይም ለመከላከል የሚቻል መሆኑን ለፕሮጀክት ባለቤት የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው፡፡

12. "Authorization" means a guarantee issued to the Proprietor that signifies the possibilities of evaluating environmental impact assessment report by the bureau to minimize and prevent environmental impact.

፲፫ “ብቃት ማረጋገጫ”የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባ ለሚሰራ አካል የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

13 "Competence Assurance" means a certificate issued to any organ working on the environmental impact assessment study report.

፲፬. “የደን አካባቢ መሥሪያ ቤት” ማለት ለደን አካባቢ ጥበቃና ልማት ቢሮ ፣ በክልል ፣ በዞን ፣ በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠዉ የመንግሥት አካል ነዉ ፡፡

14. "Forest Environment Office" means a government organ that has empowered the responsibility for Forest Environment Protection and Development Bureau at Regional, Zonal, Wereda, and City Administration levels.

፲፭. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

15. "Person" means any natural or juridical person.

**፫. የፆታ አገላለጽ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

**፬. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ማናቸውም መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ፕሮጀክቶች፣ የመንግሥት ሰነዶች እና ሰዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡ ፡

**ክፍል ሁለት**

**የተጽዕኖ ግምገማ ታሳቢዎችና ግምገማ ስለሚያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶች**

**፭. የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ድንጋጌ**

፩.ማንም ሰው የአካባቢ ተዕእኖ ግምገማ የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ፕሮጀክት ከቢሮ ይሁንታ ፈቃድ ሳያገኝ ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የአካባቢ ተዕእኖ ግምገማ ለሚያስፈልገው ማንኛውም ፕሮጀክት የሚከሰተው ተፅዕኖ ኢምንት መሆኑን ሲያምን የፕሮጀክቱ ባለቤት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲያካሄድ ላያስገድደው ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

**3. Gender expression**

In this proclamation, what is expressed in the male mesolus is also includes the female femean.

**4. Scope**

This proclamation shall applicable any public or private projects; on government instruments and persons found within the region.

**Part two**

**Projects that require impact assessment and assessment considerations**

**5. Provision of environmental impact assessment**

1. Without authorization from the bureau, no person shall commence implementation of any project that requires environmental impact assessment.

2. Without prejudice to Sub Article (1) of this Article, when bureau believes that the possible impacts of the project are insignificant, it may decide not to require the concerned Proprietor to conduct an environmental impact assessment. The detail shall be detrmined by Regulation.

፫.ማንኛውም ፈቃድ ሰጪ መስሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ፤ የንግድ ወይም ስራ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ከቢሮው ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዲሆን ይሁንታ መሰጠቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬. በዚህ አንቀዕ ንኡስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሠረት የአካባቢ ተዕእኖ ጥናት ዘገባ ተቀባይነት ማግኘቱና ከቢሮው ይሁንታ መሰጠቱ የፕሮጀክቱን ባለቤት ጉዳት ማድረስ በሚመለከት ከፍትሐብሄር ኃላፊነት ነጻ አያደርገውም፡፡

፭. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፬) እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳቱ የደረሰው በተጎጂው በራሱ ጥፋት ወይም የፕሮጀክቱ ባለቤት ኃላፊነት በሌለበት በሶስተኛ ወገን መድረሱ ከተረጋገጠ የፕሮጀክቱ ባለቤት ከተጠያቂነት ነጻ ይሆናል፡፡

**፮. ስለተጽዕኖ ግምገማ ታሳቢዎች**

በዚህ አዋጅ መሰረት የተጽዕኖ ግምገማ ሲደረግ የሚከተሉትን የተጽዕኖ መወሰኛ ነጥቦችን ታሳቢ መደረግ ይኖርበታል፤

ሀ) የፕሮጀክቱ መጠን፣

ለ) የፕሮጀክቱ ማካሄጃ ስፍራና የፕሮጀክቱ ባህሪይ

ሐ) ከሌሎች ተጽዕኖዎች ወይም ክስተቶች ጋር የሚኖረው ተደማሪነት፣

መ) የፕሮጀክቱ ቆይታ ዘመን(ጊዜ)፣

ሠ) ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ መቻሉና አለመቻሉ እና

(ረ) ክልል፣ዞን ወይም ወረዳ ተሻጋሪነቱ

3. Any licensing Office shall, prior to issuing an investment permit or a trade or an operating license for any project, ensure that the bureau has authorized its implementation.

4. In accordance to Sub Article (1) and (2) of this Article, approval of an environmental impact study report or the granting of authorization by the bureau does not exonerate the Proprietor from liability for damage.

5. Without prejudice to Sub Article (4) of this Article, exemption from liability shall be granted only when it is verified that it is the victim himself or a third party for whom the Proprietor is not responsible that has caused the damage.

6. Considerations of impact assessment

In accordance with this proclamation, the following impact determining points must be considered while undertaking the impact assessment;

a) Size of the project;

b) The project nature and the project location

c) Cumulative effect with other concurrent impacts or phenomena;

d) Duration of the project;

e) Reversibility or irreversibility

(f) Trans-regional, zonal or wereda

(ሸ) ከሌሎች ተዛማች ገፅታዎችና ቢሮው በመመሪያ ከሚዘረዘርባቸው ሌሎች ታሳቢ ሁኔታዎች፡፡

(h) Considerable situations apart from other related effects and discripitions of the Bureau directive.

፪) ፕሮጀክቱ ጠቃሚና ጎጂ ውጤቶች ካሉት ጠቃሚ ጎኑ ለሚሰፋ ፕሮጀክት ይሁንታ ይሰጣል፡፡

2) A project having both beneficial and detrimental effects; the beneficial project has authorized.

፫) የፕሮጀክቱ ጠቃሚና ጎጂ ውጤቶችን በእርግጠኝነት ማረጋገጥ ካልተቻለና አወዛጋቢ ባህሪ ካለው ቢሮው ወደ ጥንቃቄ እርምጃ በማዘንበል ፕሮጀክቱ ጉልህ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው በማለት መወሰን ይችላል::

3) The bureau shall err on the side of caution while determining the negative impact of a project having both beneficial and detrimental effects, but which, on balance, is only slightly or arguably beneficial, and thus determine that it is likely to entail a negative significant impact.

**<u>፯. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ስለሚያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶች</u>**

**7. Projects Requiring Environmental Impact Assessment**

፩)ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረተ በሚካተት በማንኛውም ፕሮጀክት ላይ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መካሄድ አለበት፡፡

1) Every project which pursuant falls in the regulation and directive issued to implement this Proclamation shall be subject to environmental impact assessment.

፪). በዚህ አንቀዕ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ደንብና መመሪያ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው ስለሚታሰቡና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸውን ፕሮጀክቶች ለይቶ ማመልከት አለበት፡፡

2). Any regulation and directive listed under Sub Article (1) of this Article shall, among other things, determine categoris of projects not likely to have negative impacts, and so do not require environmental impact assessment;

**<u>፰. ክልል ፣ ዞን ወይም ወረዳ ተሻጋሪ የአከባቢ ተፅዕኖ ግምገማ</u>**

**8. Trans-regional, zonal or Woreda environmental impact assessment**

፩. ማንኛውንም የፕሮጀክት ባለቤት ክልል ፣ ዞን ወይም ወረዳ ተሻጋሪ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሲያካሄድ ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል ተብለው የሚገመቱ በ የትኛውም ዞን ወይም

1. A Proprietor shall carry out the environmental impact assessment of a project that is likely to produce a trans-regional; trans-zonal or wereda impact in consultation with the communities likely to be affected in any zone

፪. ክልል ፣ ዞን ወይም ወረዳ ተሻጋሪ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት በሚካሄድበት ክልል፣ ዞን ወይም ወረዳ ሥር የሚገኝ የአካባቢ መስሪያ ቤት ለቢሮው የአከባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ እንዲቀርብ ማድረግ አለበት።

፫. ቢሮው በዚህ አንቀፅ ንዕስ አንቀፅ (፪) መሰረት የቀረበለትን ዞን ወይም ወረዳ ተሻጋሪ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት ዘገባን መመርመር ከመጀመሩ በፊት ጉዳት ይደርስባቸው ይሆናል የሚባሉትን የሚመለከታቸውን አካባቢ ማህበረሰቦች አስተያየት የተካተተ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

፬. በክልል ፣ በዞን ፣ በወረዳዎችና በከተማ አስተዳደር የ ደን አካባቢ ጥበቃና ልማት ቢሮ የሚፀድቁ ፕሮጀክቶች ዓይነት በቢሮው ይወሰናሉ።

## ክፍል ሶስት

## ስለአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ፣ ምርመራ እና ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

### ፱. ስለአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ

፩. ማንኛውንም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ መሆን ይኖርበታል።

ሀ. የፕሮጀክቱን ስም፣ባህሪ፣በጥቅም ላይ የሚውለውን ቴክኖሎጂና አጠቃቀም፣

ለ.ፕሮጀክቱ ሲተገበር እንዲሁም ቋሚ ስራው ሲከናወን ወደ አካባቢ የሚለቀቀውን የበካይ ይዘትና መጠን፣

2. The environmental bureau in the region, zone or woreda where a project with likely trans-regional; trans-zonal or woreda impact is being initiated shall ensure the submission of the environmental impact study report of the project to the Bureau.

3. In accordance with the Sub Article (2) of this Article, the Bureau shall, prior to embarking on the evaluation of submitted impact study report of a project with likely trans-zonal or wereda, ensure that the communities likely to be affected in each zone have been consulted and their views incorporated.

4. The Bureau determines the type of projects approved by Regional, Zonal, Woreda, and City administration Forest Environment Protection Development Bureau.

## Part three

## Assessment and Validity of Environmental Impact Study Report

### 9. Report of Environmental Impact Study

1. Any environmental impact Assessment shall contain a description of:

A. The name and nature of the project, including the technology and processes to be used;

B. The content and amount of pollutant that will be released during project impelemtation as well as during operation;

ሐ. የስራው እንቅስቃሴ የሚጠይቀውን የሀይል ፍጆታና ምንጭ፣

መ. ሊከተል ስለሚችል ዘን ወይም ወረዳ ተሻጋሪ የአከባቢ ተፅዕኖ መረጃ፣

ሠ. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይከተላሉ ተብለው የተገመቱ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖዎች ባህሪያትና የሚቆዩበት ጊዜ፣

ረ. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይከተላሉ ተብለው የተተመኑ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖዎች ባህሪያትና የሚቆዩበት ጊዜ፣

ሰ. የአካባቢ አያያዝ ችግርን ለማቃለል የተነደፉ እቅዶችና የአደጋ መከላከያ ዝግጁነት፣

ሸ.ፕሮጀክቱ በሚተገበርበትና ቋሚ ስራው በሚከናወንበት ወቅት የውስጥ ቁጥጥርና የክትትል ስራዎች የሚካሄድባቸውን መንገዶች፣

ቀ. ሌሎች በደንብና መመሪያ ላይ የሚዘረዘር ተጨማሪ ዘገባ ሊያካትት ይችላል፡፡

፪) ቢሮው የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባን ለማዘጋጀትና ዘገባውን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመመርመር የሚያስችል ዝርዝር ማኑዋል ወይም መመሪያ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

፫) የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት ዘገባ ማንም ሊረዳው በሚችል ግልጽ ቋንቋ በአጭሩ የተዘጋጀ ሆኖ የጥናቱን መግለጫና መረጃ አሟልቶ የያዘ መሆን አለበት፡፡

c. Source and amount of energy required for operation;

d. information on likely trans-zonal or werda environmental impact;

e. characteristics and duration of all the anticipated direct or indirect, positive or negative impacts;

F. characteristics and duration of all the estimated direct or indirect, positive or negative impacts;

G. proposed plans to mitigate environmental management problem and contingency plan in case of accident; and

H. procedures of self auditing and monitoring during implementation and operation

Q. other additional report described on the regulation and directive shall be incorporated

2) The Bureau shall prepare a detailed manual or directives that allows the preparation and effective evaluation of environmental impact study report

3) An environmental impact study report shall include precisely prepared non-technical terms that anyone can understand and complete statement as well as information of study.

## ፲. ስለአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ምርመራ

፩. ማንኛውም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልገው ፕሮጀክት የአከባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ከፕሮጀክቱ ተግባር አስቀድሞ ለምርመራ ለቢሮው መቅረብ አለበት፡፡

፪. ቢሮውም የቀረበለትን ዘገባ የሕዝብ አስተያየትና የባለሙያዎችን ሀሳብ በመመዘን እስከ ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

፫. ቢሮው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሰረት የሚሰጠው ውሳኔ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡

ሀ. ፕሮጀክቱ ጎጂ ተፅዕኖ እንደማያስከትል ካመነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፕሮጀክቱን ይቀበላል፤ እንዲተገበርም ይሁንታውን በፅሁፍ ይሰጣል፡፡

ለ. አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስቀረት ወይም በበቂ ሁኔታ ለመቋቋም የሚቻል መሆኑን ካመነ ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት ወይም ጉዳቱን ለመቀነስ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ዘርዝሮ እንዲያሟሉ ያደርጋል፡፡ የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ ተሟልቶ ሲቀርብለት ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታውን በፅሁፍ ያሳውቃል፡፡

ሐ. ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ቢደረግ አሉታዊ ተፅዕኖው የከፋ ከሆነና በአጥጋቢ ሁኔታ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ እንደማይቻል ካመነ ትግበራውን ይከለክላል፤ ክልከላውንም በፅሁፍ ያሳውቃል፡፡

## 10. Reviewing of the environmental impact study report

1. Prior to its implementation, any project that requires environmental impact assessment shall submit environmental impact study report to the bureau for review.

2. Taking into account any public comments and expert opinions, within 15 working days, the bureau shall give a decision to the submitted report.

3. In accordance with Sub Article (2) of this Article, the Bureau shall give one of the decisions listed hereunder:

A. approve the project without conditions and issue authorization in written manner if it is convinced that the project will not cause negative impacts;

B. approve the project and issue authorization in written manner with conditions that must be fulfilled in order to eliminate entirely or reduce adverse limpacts or reduce adverse impacts to insignificance if it is convinced that the negative impacts can be effectively countered,

C. If the negative impact of the project is severe and cannot be satisfactorily avoided or mitigated, the project will be prohibited and the prohibition will be announced in writing.

**፲፩. የፀደቀ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ**

፩. የይሁንታ ፈቃድ ያገኘ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ይሁንታ በተሰጠበት ሰነድ ላይ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተተገበረ ተቀባይነቱ ይቀራል፡፡

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት ተቀባይነት ያጣ የፕሮጀክት ባለቤት በጊዜ ገደቡ መተግበር ያልተቻለበትን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር አጋጥሞት ከሆነ ወይም ሌላ ቅሬታ ካለው ተቀባይነቱ ውድቅ መደረጉን መ/ቤቱ በጹፍ ካወቀበት ቀን አንስቶ ባለው ፲ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቢሮው ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ጥያቄው የቀረበለት ቢሮው በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ የዘገባው ተቀባይነት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዲራዘም ወይም ዘገባው እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲካሄድ መወሰን ይኖርበታል፡፡

፬. ቢሮው በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት የተቸገረበት ልዩ ሁኔታ ካጋጠመው በተጨማሪ ፲፭ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን መስጠት አለበት፡፡

**፲፪. የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ውድቅ መሆን ስለሚያስከትለው ውጤት**

፩. በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲ ንዑስ አንቀፅ ፫(ሐ) መሰረት ውድቅ የተደረገ ፕሮጀክት በምንም ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም፡፡ በቢሮው ውድቅ የተደረገን ፕሮጀክት ተግብሮ የተገኘ የፕሮጀክት ባለቤት አግባብ ባለው የወንጀልና የፍትሐብሄር ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**11. The Validity date of approved environmental impact study report**

1. An Authorized environmental impact study report shall expire if the project has not been implemented according to the time frame set during its authorization.

2. A Proprietor, pursuant to Sub Article (1) of this Article, shall submit difficulties prevented timely implementation or has other grievance to the Bureau within ten consecutive working days from receipt of written notification of the rejection.

3. Within 30 days from the receipt of an application pursuant to Sub Article (2) of this Article, the Bureau shall decide whether to extend or revise or redoing of the validity of the report.

4. The Bureau shall issue a decision within 15 additional days if challenged with special circumstance to issue a decision with 30 working days.

**12. Consequences of rejection of the environmental impact study report**

1. Project Rejected pursuant to Sub Article 3(c) of Article 10 of this proclamation can't be implemented; any Proprietor, who implements the project rejected by Bureau, will be liable in accordance with appropriate criminal and civil law.

፪. የፕሮጀክት ትግበራ የጊዜ ገደብ በማለፉ ምክንያት ውድቅ የተደረገ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፩ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ጥያቄ አቅርቦ ጊዜው እንዲራዘም ወይም እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲካሄድ ቢሮው ካልፈቀደ ይሁንታው እንዳልተሰጠ ይቆጠራል፡፡

**፲፫. ስለአዲስ ሁኔታ መከሰት**

፩. ይሁንታ አግኝቶ ወደ ትግበራ የገባ ፕሮጀክት በትግበራ ሂደት ከባድ እንድምታ ያለውና ቀደም ሲል ያልተጠና እውነታ ቢከሰት ቢሮው እንድምታውን ለማጤን እንዲቻል የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው እንደ አስፈላጊነቱ እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲካሄድ ማድረግ ይችላል፡፡

፪. የፕሮጀክቱ ባለቤት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት አዲስ ሁኔታ መከሰቱን እንዳወቀ ለቢሮው የማሣወቅ ግዴታ አለበት፡፡

**ክፍል አራት**

**ስለትግበራ ክትትል ፣ የመንግሥት ሰነድ ፣ የፕሮጀክት ባለቤቶችና የቢሮው ግዴታዎች**

**፲፬. ስለትግበራ ክትትል**

፩. የፕሮጀክቱ ባለቤት የፕሮጀክቱን ትግበራ በተሠጠው ይሁንታ መሠረትና ከተጣለበት ግዴታ አንፃር በአግባቡ እየተገበረ መሆኑን ክትትል ቢሮው ማድረግ አለበት፡፡

2. Environmental impacts study report that has been rejected due to expiration pursuant to Sub article (2) of Article (11) of this proclamation, request submitted for extension or revision or redoing, if the Bureau will not permit, authorization has not be considered as issued.

**13. Occurrence of New Circumstance**

1. If an unforeseen fact of serious implication is realized, during the implementation process, on the project that has been started implementation having aouthorization; the bureau may, as may be appropriate, make the environmental impact assessment to be revised or to be redone in order to address the implication.

2. Pursuant to Sub article (1) of this Article, the Proprietor is obligated to notify the bureau immediately upon the occurrence of any new circumstance.

**Part four**

**Monitoring of Implementation, Public Instrument, Proprietors, and Bureau Obligations**

**14. Monitoring of implementation**

1. The bureau shall monitor if the Proprietor is carrying out the implementation of an authorized project in compliance with the obligation imposed and granted authorization.

፪. ቢሮው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ክትትል ሲያደርግ በተጣለበት ግዴታ መሠረት ወይም ይሁንታውን በገኘበት መሠረት ካልሆነ የሚታረምበትን አግባብ በመዘርዘር የእርምት እርምጃ እንዲወስድ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

፫. በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት የእርምት እርምጃ ባልወሰደ ወይም መውሰድ ባልፈለገ የፕሮጀክት ባለቤት ላይ ቢሮው ይሁንታውን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

**፲፭. የይሁንታ መሰረዝ ስለሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት**

፩. በዚህ አዋጅ ወይም ይህን አዋጅ ተከትለው በሚወጡ ደንብና መመሪያ መሠረት የፕሮጀክት ይሁንታ ሲሰረዝ ይሁንታው እንዳልተሰጠ ይቆጠራል፡፡

፪. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ ንኡስ አንቀጽ (፫) መሠረት የፕሮጀክት ይሁንታ ቢሰረዝም ፕሮጀክቱ ያደረሰው ጉዳት ካለ የፕሮጀክቱ ባለቤት አግባብ ባለው የፍትሐብሄር ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፲፮. ስለ መንግሥት ሠነድ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ**

፩. በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው ደንብ ወይም መመሪያ ላይ በተገለጸውና በሚገለጸው መደቦች ውስጥ የሚካተት ማንኛውም የመንግሥት ሰነድ ከመጽደቁ በፊት የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ መደረግ አለበት፡፡

2. A failure to implement the authorized project in compliance with the obligations imposede, the bureau, while monitoring, may issue a written warning to undertake specified rectification measure pursuant to Sub article (1) of this Article.

3. The bureau shall suspend or cancel the authorization of the Proprietor who fail to take or not willing to undertake the rectification measure issued pursuant to the warning.

**15. The Legal Cosnequence of Canciling of Authorization**

1. Authorization of the project is not considered as issued when it will be canceled pursuant to this proclamation or regulation and directive issued following this proclamation herein.

2. Even if the authorization is canceled pursuant to Sub Article (3) of Article 14 of this proclamation, the Proprietor will be liable in accordance with the relevant civil law if the project casued any damage.

**16. Environmental Impact Assessment of Public Instrument**

1. A public instrument included in the category of this proclamation and regulation or directive issued following this proclamatin herein, shall, prior to approval, be subject to environmental impact assessment.

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገ ቢኖርም በባህሪያቸው ቸል ሊባል የማይችል አካባቢያዊ ተጽዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው የሚገመቱ የመንግሥት ሰነዶች መደብን ለመለየትና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲካሄድባቸው ለማድረግ የሚያስችል ልዩ መመሪያ ቢሮው ሊያወጣ ይችላል፡፡

፫. ማንኛውም የመንግሥት አካል የሚያዘጋጀው ማናቸውም የመንግሥት ሰነድ ሊያስከትለው የሚችለው ተጽዕኖ እንዲገመገም ለማስቻል ከቢሮው ጋር መተባበር አለበት፡፡

፬. በዚህ አዋጅ መሠረት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ያልተካሄደበትን ፕሮጀክት ተግባራዊ የሚያደርግ መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ወይም የተቋሙ ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ፲፯. ስለፕሮጀክት ባለቤት ግዴታዎች

፩. አንድ የፕሮጀክት ባለቤት የፕሮጀክቱን የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አካሂዶ ፣ የፕሮጀክቱን የአካባቢ ተጽዕኖዎች ለይቶ እና ተጽዕኖዎችን የማስቀረያ ወይም የመቋቋሚያ ዘዴን በጥናቱ አካቶ ለቢሮው ተገቢነታቸውን ከወሰነባቸው ሰነዶች ጋር ዘገባውን ማቅረብ አለበት፡፡

፪. በፕሮጀክቱ ላይ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ የሚካሄድባቸውና ዘገባው የሚዘጋጀው ቢሮው ወይም በፌደራል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፣ ደንና አካባቢ ጥበቃና ልማት ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ላይ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን በሚያሟሉ ባለሙያዎች መሆኑን የፕሮጀክት ባለቤቱ ማረጋገጥ አለበት፡፡

2. Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this article, the Bureau shall issue special directive to determine the category as of public instruments which are likely to entail significant environmental impact and the procedure of their impact assessment.

3. Any government organ shall collaborate with the Bureau to enable the evaluation of likely environmental impacts of any public instrument prepared by it.

4. Pursuant to this proclamation, a public as well as private institution or head of the institution that commence the implementation of a project without a prior to environmental impact assessment shall be laible.

## 17. Duties of a Proprietor

1. A Proprietor shall undertake an environmental impact assessment, identify the project impacts, incorporated the means of their prevention or containment, and submit to the bureau the environmental impact study report together with the relevant documents.

2. A Proprietor shall ensure that the environmental impact of his project is conducted and the environmental impact study report prepared by experts that meet the requirements specified under any directive issued by the Bureau or Federal Environmental Protection Authorit or Bureau of Forest Environment Protection Development Bureau.

፫. የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማና የጥናት ዘገባ ለማዘጋጀት የሚያስፈልገው በጀት በፕሮጀክት ባለቤቱ መሸፈን አለበት።

፬. አንድ የፕሮጀክት ባለቤት ፕሮጀክቱን ሲተገብር በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ የተዘረዘሩ ግዴታዎችን ማሟላት አለበት።

3. The cost of undertaking an environmental impact assessment and preparing an environmental impact study report shall be borne by the Proprietor.

4. When implementing his project, a Proprietor shall fulfill the terms and condition of authorization.

## ፲፰. ስለ ቢሮው ግዴታዎች

## 18. Duties of the Bureau

፩. ይህንን አዋጅና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣውን ደንብና መመሪያ ለሕዝብ የማሰተዋወቅ፤

፪. ከፕሮጀክት ባለቤቶች የሚቀርቡ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ምርመራ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ በመፈፀም ውሳኔውን በወቅቱ የማሳወቅ፤

፫. ከሀገሪቱ የትኩረት አቅጣጫና አግባብነት ባለው የኢንቨስትመንት ሕግ መሰረት ምላሽ ማግኘት የሚገባውን ፕሮጀክት ምክንያታዊ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ተገቢ ምላሽ የመስጠት፤

፬. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማና ጥናት ለማድረግ የሚረዱና ከዘርፉ ቴክኖሎጂ ጋር የሚጣጣም የአሰራር ማኑዋል የመቅረፅ ፤ የመተግበር፤

፭. በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማና ጥናት የሕዝቡን ተሣትፎ የማጎልበትና በየአካባቢው የሚፈቀዱ ፕሮጀክቶች ላይ ሕዝቡ እንዲያውቀውና እንዲሳተፍበት የማድረግ፤

1. Disseminating this proclamation, and regulation and directive issued following this proclamation to the public;

2. Undertaking the review of environmental impact study report submitted by the Proprietor within a timeframe and promptly communicating the decision;

3. Giving seemly response to a project that shall entail response pursuant to country's priorities and relevant investment law within a reasonable timeframe;

4. Designing and implementing operational manual that aligned with the latest technology and important to undertake environmental impact assessment study;

5. Capacitating public participation in the environmental impact assessment study and let the public to notice and participate the projects that will be permitted;

፮. የተጎዳ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ ወይም ብክለትን ለማስቀረት ወይም የተበከለን አካባቢ ለማጽዳት አቅሙ በሚፈቅደው መሰረት የፕሮጀክቱን ባሌቤት የማማከር ፣ የቴክኒክ ወይም የማስገደድ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

## ፲፱. የፌዴራል መንግሥት ስልጣንና ከክልሉ ጋር ያለው ግንኙነት በተመለከተ

፩. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራል አካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን በፌደራሉ አዋጅ መሰረት ፡-

ሀ/ ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ ፕሮጀክቶች፣

ለ/ የፕሮጀክቱ ባለቤት የፌደራል መንግሥት የሆኑ ፕሮጀክቶች እና

ሐ/ ሀገራዊ ፋይዳቸው በላቀና አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት የፌደራል ደን አካባቢ ጥበቃና ልማት መሥሪያ ቤት እንዲቆጣጠራቸው ለተወሰኑ ፕሮጀክቶች ፈቃድ የመስጠት ፣ የመተግበርና ቁጥጥር የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ከፌደራል አካባቢ ጥበቃና አየር ንብረት ለውጥ ጋር በትብብር መስራትን ወይም በውክልና መስራትን አይከለክልም፡፡

፫. ቢሮው ክልላዊ ለሆኑ ፕሮጀክቶች ፈቃድ የመስጠት ፣ የመተግበርና ቁጥጥር የማድረግ ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ በዞንና በወረዳ ደረጃ በሚገኙ መዋቅሮቹ የሚፈጸሙ ተግባራትን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

6. As feasible, the Proprietor shall be consulted, provide technical assistance, or have obliged duty to rehabilitate a damaged area, prevent pollution, or clean up a polluted area.

## 19. Regarding the authority of the federal government and its relationship with the region

1. Subject to the provisions of this Proclamation, the Federal Environment and Climate Change Authority, in accordance with the Federal Proclamation:

A/ projects that is likely to have trans-regional environmental impact,

B/ Projects where the Proprietor is the federal government and

C/ Pursuant to the relevant law that has a siginificant contribution to the nation, the Federal office of Forest Environment Protection Development shall have the responsibility of issuing permission, implementing, and monitoring the projects which are decided to be monitored by the Authority .

2. Despite the provision of Sub-Article (1) of this Article, working in collaboration with Federal Environment Protection Climate Change, or through delegation is not prohibited.

3. Without prejudice to Bureau's responsibility of issuing permission, implementing, and monitoring regional projects; through directive, shall determine the activities to be implemented by its structures found at Zonal and Woreda level.

## ፳. የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት

፩. ለፕሮጀክት ትግበራ በተሰጠ ይሁንታ መሠረት በክትትል ወቅት ወይም ፕሮጀክቱን በሚመለከት በተሰጠ ማንኛውም ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ለቢሮው ኃላፊ ቅሬታውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡ በውሳኔው ካልረካ ወደ ፍ/ቤት መሄድ ይችላል፡፡

፪. በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማና ጥናት ላይ ፕሮጀክቱ የሚተገበርበትን አካባቢ ሕዝብን ቢሮው አላሳተፈም የሚል ቅሬታ ያለው ማንኛውም ያገባኛል የሚል ሰው አቤቱታውን ለቢሮው በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የቢሮው ኃላፊ ውሳኔውን በሰላሳ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ መስጠት ይኖርበታል፡፡

## ፳፩. ስለ ቅጣት

፩. አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ይህን አዋጅና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብና መመሪያ መጣስ ያስቀጣል፡፡

፪. ማንኛውም የፕሮጀክት ባለቤት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ እንዲካሄድበት የተደነገገበትን ማንኛውንም ፕሮጀክት የቢሮውን ይሁንታ ሳያገኝ የተገበረ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማያንስ ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ እስራትና ከብር ሁለት መቶ ሺህ በማያንስ ከብር አምስት መቶ ሃምሳ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፳. Grievance Procedure

1. Any person dissatisfied with the authorization or monitoring or any decision regarding the project may submit a grievance notice to the head of the Bureau. If dissatisfied with the decision, he may go to court.

2. Anyone who has grievance that the Bureau did not involve the local community of the vicinity where the project is to be implemented in the environmental impact assessment and study may submit his complaint notice to the Bureau.

3. The decision of the head of the bureau shall, as provided under Sub Article (1) and (2) of this Article, be issued within 30 days following the receipt of the grievance.

## 21. Penalties

1. Unless a severe penalty is prescribed by the relevant criminal law, violation of this proclamation, and regulation as well as directive issued following this proclamation shall incur penalty.

2. Any Proprietor who implements a project, for which an environmental impact assessment is enshrined, without obtaining authorization from the bureau, shall be penalized with imprisonment of not less than five years and liable to a fine of not less than one hundred thousand Birr and not more than five hundred fifty thousand Birr.

ሀ/ ከጉዳቱ አንጻር ከአምስት እስከ አስር አመት ጽኑ እስራትና ከብር ሁለት መቶ ሺ እስከ አምስት መቶ ሺ ወይም በሁለቱም ይቀጣል ፡፡

፫. ማንኛውም የፕሮጀክት ባለቤት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ዘገባ ውስጥ ሀሰተኛ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ ከሁለት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ከሦስት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም በቀረበው ሀሰተኛ መግለጫ ምክንያት ጉዳት ደርሶ ከሆነ ከአራት ዓመት በማያንስና ከስድስት ዓመት በማይበልጥ እስራትና ከሁለት መቶ ሺ በማያንስ አራት መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፭. ማንኛውም የሙያ ብቃት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃድ ሲሰጠው በግልጽ የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ ወይም ተፈላጊ ዝርዝሮችን በመዝገብ ሳያሰፍር ከቀረ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከብር አንድ መቶ ሺህ እስከ ሦስት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፮. ከዚህ በላይ በእስራት የሚያስቀጡ ጥፋቶችን የፈጸመው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ የእስራት ቅጣቱ የድርጅቱን ኃላፊና ሌሎች በየደረጃው ያሉ የድርጅቱ ኃላፊዎች እንደ ተሳትፊአቸው ሁሉንም የሚመለከት ይሆናል፡፡

A/ Based on the damage inflicted, the person shall be penalized with imprisonment of solitary ten years and liable to a fine of two hundred thousand Birr to five hundred thousand Birr, or both.

3. Any Proprietor who makes false presentations in an environmental impact assessment study report shall be penalized with imprisonment of not less than two years and not more than five years, and liable to a fine of not more than three hundred fifty thousand Birr.

4. Despite the provison of Sub Article (3) of this Article, the Proprietor will be penalized with imprisonment of not less than four years and not more than six years and liable to a fine of not less than two hundred thousand Birr if the damage inflicted is due to the submitted false presentation.

5. Any person who, issued professional competence license, fails to keep the required records or to fulfill conditions of authorization issued, as the extent of offence, shall be liable to a fine of Birr from one hundred thousand to three hundred thousand.

6. Where the offences that likely causes penalty of imprisonment are committed by a juridical institution, the penality shall involves head of the institution and, as per their involvement, all other heads of the institution found in each position of the hierarchy.

፯. በዚህ አንቀጽ መሰረት በወንጀል ኃላፊነት መቀጣት እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የፍትሐብሄር ሕግ መሰረት የጉዳት ካሳ ኃላፊነትን አያስቀርም፡፡

7. Without prejudice to penalty of being liable to crime pursuant to this Article, compensation of the damage does not exempt the liability.

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## Part five

## Miscellaneous provisions

### ፳፪. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ ተፈጻሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 22. Duty to cooperate

Any person shall have the duty to cooperate for implementation of this Proclamation.

### ፳፫. ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም አሰራር በዚህ በተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈፃምነት አይኖረውም፡

### 23. Inapplicable laws

Any law or practice inconsistent with this Proclamation is inapplicable regarding matters provided herein.

### ፳፬. ደንብ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 24. Power to issue regulation

The Executive Council of the regional State may issue regulations for the implement of this proclamation.

### ፳፭. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቢሮው ይህን አዋጅ ተከትሎ የሚወጣ ድንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 25. Power to issue directives

The Bureau may issue directives for the implementation of regulations issued following this Proclamation.

### ፳፮. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምከር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ታህሳስ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

### 26. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the 15th day of December, 2023

**አርባ ምንጭ ታህሳስ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ጥላሁን ከበደ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር**

**Done at Arba Minch, this 15th day of December, 2023.**

**Tilahun Kebede**

**Chief Executive of The South Ethiopia Regional State**